ነጻነት ምድን ነው ? የነጻነት ዋጋው ስንት ነው ?

(ከኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር )

ነጻነት ፣ እኩልነት ፣ አንድነት ፣ ጠባብነት ፣ ትምክህተኛነት ፣ ኢትዮጵያዊነት የተሰኙት ቃላት በዚህ ወቅት ከምንም በላይ የሚነሡ የወቅቱ አሳብ ገላጭ ቁልፍ ቃልት ሁነው ታይተውኛል ። ለመሆኑ እነዚህን ቃላት የሚጠቀሙ ሰዎች ሁሉ እነዚህን ቃላት በእውነተኛ ትርጉማቸው ተረድተው ፣ በተገቢው ቦታ ቃላቱ የሚወክሉትን መሠረተ ሐሳብ ለመግለጽ ነውን  የሚጠቀሙባቸው ? ወይስ ሲባል ሰምተው ነው የሚያስተጋቡአቸው ? እያልኩ ማሰብ ጀመርኩ ።   ይልቁንም Sep 20/16 የተላለፈው የESAT ራድዮ ሳዳምጥ ልብ የሚነካ ፣ ነጻነት የሌላቸውን ወገኖቼን ጩኸት የሚያስተጋባ ፣ በእንባ የታጀበ ፣ ልብ የሚሰብር ቃለ መጠየቅ ሰማሁ ። ይህ ሰው በሕወሀት ወታደሮች ታፍኖ ከብዙ ልጆች ጋር 9-10 ሰዓታት በመኪና ተጓጉዞ ቤንሻንጉል ጉምዝ ውስጥ ለቍጥር የሚያታክቱ ወጣቶች በሞትና በሕይወት መካካል ወዳሉበት የሥቃይ ቦታ መወሰዱን ይናገራል ። በቁጥጥር ሥር የዋሉት ያለፍትሕ የታሰሩት ወንድሞቻችን ድንጋይ ሲፈልጡ ውለው የሚመገቡት እንደ ሌላቸው ፣ ብዙዎቹ በድብደባ ብዛት ራሳቸውን የሳቱ እንደ ሆኑ ይመሰክራል ። ቢሞቱ እንኳ ቀባሪ እንደ ሌላቸው ከሲቃ ጋራ ይናገራል። እርሱንም አንድ የሚያውቀው ወታደር በሌሊት አሾልኮ በመኪና ሸኝቶ እንዲያመልጥ እንደ ረዳው ሲናገር አደመጥኩ ፤ የሚናገርበት ድምጽ ነጻነት የሌለው ዜጋ ፣ የተጠቃ ትውልድ ድምጽ ምን እንደሚመስል በግልጽ ያሳያል ። ከአሁን አሁን ገድለው ቱቦ ውስጥ ሊጥሉት እንደሚችሉ እንደሚያስብ ይናገራል ፤ ምሥጢር አወጣህ ተብሎ የሚመጣበትን መከራ ቢያውቅም ስለ ወንድሞቹ መናገርን መምረጡን ይገልጻል ።

ስለታሰሩት ወጣቶች ሥቃይ  ሲናገር - በወታደር ተከበው ፣ ራሳቸውን ተላጭተው ፣ ሙሉ ቀን ድንጋይ ሲፈልጡ ይውላሉ፣ ልጆቹ ያሉት ቤንሻንጉል ጉምዝ ጫካ ውስጥ ነው ፣ ውጡና ሂዱ እንኳ ቢሉአቸው ወጥተው መሄድ ከማይችሉበት ጫካ ውስጥ ነው የተጣሉት ፤ በሽታና ረኃብ እየፈጃቸው ነው ። ብዙዎቹ በድብደባ አእምሮቸውን ስተዋል ፣ አይሰሙም አይለሙም ፤ ቢሞቱም ቀባሪ የላቸውም ፤ ጉንዳን ነው የሚበላቸው ፤ ልጆቹ ከጎንደር ፥ ከባሕርዳር ፥ ከጭልጋ የመጡ ናቸው ፤ እነዚህ ወጣቶች በረኃብ ሊሞቱ ይችላሉ ፣ ምን ብየ ለማን እንደማወራ ፣ ምን ብየ እንደምናገር አላውቅም ። ሁኔታው ከባድ ነው» እያለ ስሰማው ለሰው ልጅ ነጻነቱን ከሚነጥቀው የበለጠ ባላጋራ እንደሌለው ተሰማኝ ። አንባቢዎች ይህን ነጻነት ያጣች ነፍስ ልቅሶና ጩኸት መስማት ትችላላችሁ? ። [i]

ብዙ አዘንኩ ወደ እግዚአብሔርም ስለ ተጠቁት ጸለይኩ ፤ ይህ ሁኔታ ብዙ እንዳስብ ምክንያት ሆነኝ ። እንዲህ እያልኩ :- ለመሆኑ ነጻነት ምንድ ነው ? የነጻነትስ ዋጋው ስንት ነው ? እኩልነትስ ማለት ምን ማለት ነው ? አንድነት ማለት ምን ማለት ነው ? አንድነትስ የሚጠቅመው ማንን ነው ? በሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት የሚያምኑ ዜጎችስ ስለ አንድነት መክፈል ያለባቸው ዋጋ ምን ያህል ነው ? ጠባብነት ምንድን ነው ? ጠባብስ ማን ነው ? ትምክህት ማለት ምን ማለት ነው ? ትምክተኛስ ማነው ? ኢትዮጵያዊነት የሠለጠነበት ሕሊና ባለቤት መሆን ትምክት ነውን ? ከሆነስ ጉዳት አለውን ? የሚሉትን ጥያቄዎች አእምሮየ ሲያወጣ ሲያወርድ ከቆየ በኋላ አሳቤን ለአንባያን ለማካፈል ስወስን መጀመሪያ ስለ ነጻነት ልጽፍ ወሰንኩ ፤ ዛሬ ነጻነት ምንድን ነው ? ነጻነትስ የሚያስከፍለው ዋጋ ስንት ነው ? የሚሉትን ነጥቦች በአጭሩ እናያለን ።

<u>**ነጻነት ምድን ነው**</u>?

1) ነጻነት ማለት ለማንኛውም ሰው በተፈጥሮ የተሰጠውን ሕይወት ያለግዳጅ የመኖር ፣ በተፈጥሮ በተሰጠው አእምሮ የማሰብ ፣ ያሰበውን የመናገር ፣ የመጻፍ ፣ ላመነበት ነገር የመሰብሰብ ፣ በነጻነት የማምለክ ፣ ይጠቅመኛል ያለውን የማድረግ ፣ አይጠቅመኝም ያለውን የመተው መብት ነው ። ለመንግሥት  ይህንን የዜጎችን ነጻነት ማክበር የመጀመሪያ ተግባር መሆን ነበረበት ። ሰውን ፈጥሮ የሚገዛ አምላክ ይህንን የሰውን የነጻነት መብት ተጋፍቶ አያውቅም ። በአደጉት አገሮች የነጻነት መብት ትርጉም ሰፍቶ የሰው ልጅ የዕለት ምግብ ፣ መጠለያና ልብስ እንዲሁም ሕክምና የማግኘት መብት አለው ።

በሀገራችን ነጻነት የለም ስንል ከላይ የተዘረዘሩት የሰው ልጅ የተፈጥሮ መብቶች በመሣሪያ ኃይል በሚገዛው የሕወሓት መንግሥት ከሕዝቡ ላይ ተወስደዋል ማለታችን ነው ። ሕዝብን እና ሕወሓትን ሆድና ጀርባ ያደረጋቸው ፥ ይህ የተፈጥሮ የነጻነት ሕግ በጉልበት ስለ ተደመሰሰ ነው ።  ነጻነት ቅንጦት አይደለም ፣ ነጻነት ህልውና ነው ። ነጻነት ሰው መሆን ሲሆን ፥ነጻነትን መግፈፍ ሰውን ከሰውነት ውጭ ማድረግ ነው ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን እንደሚያስብ መንግሥት የማወቅ ችሎታ ስለሌለው እንጂ ቢችል ኑሮ ሕዝቡን በሰልፍ አቁሞ ለምን እንዲህ ታስባላችሁ እያለ በጥይት ከመደብደብ ወደ ኋላ የሚል አይመስለኝም ።

ይህም የሚታወቀው ያሰቡትን ደፍረው የተናገሩ የጎንደር ፥ የጎጃም ፥ የኦሮሞ ወጣቶችን በጥይት እይመታ የጣላቸው ፣ በዱላ ሰባብሮ ፥ ጠጉራቸው ላጭቶ ፥ ድንጋይ እያስፈለጠ በረኃብ እየቀጣ ፣ በርሃ ጥሏቸዋል ። የወልቃይትን

የጠገዴን አማሮች የሀውና ያለማቋረጥ ለ25 ዓመታት ይጨፈጭፏቸዋል፤ ንብረታቸውንና ቤታቸው ያቃጥልባቸዋል ፣ ያመለጡትን ያሳድዳል ፣ የያዛቸውን ሌትና ቀን ያሰቃያቸዋል ። ነጻነት ማጣት በተግባር ይህን ሲመስል ፣ የሰው ልጅ ለነጻነት ያለውን ፍላጎት ብርታት የሚያሳየን ይህን ሁሉ ተቋቁሞ ከታጠቁ እና ከሠለጠኑ የሕወሀት ወታደሮች ጋር ገበሬው ሕዝባቸን በሚከፍለው የሕይወት ዋጋ በገሀድ ይታያል ።

2) ነጻነት የሚለውን ቃል የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ምን ብሎ እንደ ፈታው ለማየት ስመለከት ነጻነትን በመተርጎም ፈንታ «ባርነት» የሚለውን ይመልከቱ ብሎ አልፎት አየሁ ። [ii] በዚህ ጊዜ የነጻነት ትርጉም የበለጠ ተገለጠ ፤ ነጻነት የባርነት ተቃራኒ ነው ፤ ባርነት በራስ ሕይወት አለማዘዝ ፥ በራስ ፈቃድ አለመኖር ፥ የሌላ መጠቀሚያ እቃ መሆን ነው ። ነጻነት ደግሞ ከዚህ ሁሉ ነጻ ሁኖ መኖር ነው ። ሕዝባችን ነጻነት ከሌለው እንደ ክላሽ እንደ መትረጌስ ማንም የሚያጮኸው ፣ እንደ መኪና ማንም የሚዘውረውና ወደ ፈቀደው የሚያሽከረክረው ይሆናል ። በእኔ ግንዛቤ ሕወሀት ከሕዝቡ ጋር የተጣላው ይህን በማድረጉ ነው እንጂ ከትግራይ በመፍለቁ አይደለም ። የትግራይንም ሕዝብ በክፉ እያስነሡት ያሉ የሕወሀትን ክፉ ተግባርና የሕወሐትን አገር ገዳይ መመሪያ እየተቀበሉ የሕዝብን ንብረት የሚያቃጥሉ ፣ ሕዝብን በሀገሩ ላይ አላኖር ያሉ የትግሬን ሕዝብ የማይወክሉ ትግሬዎች ናቸው ። በዚህ ወቅት የኢትዮጵያን ሕዝብ ደስታና ኀዘን አብረው ለዘመናት ሲካፈሉ የኖሩ ንጹሐን ትግሬዎች ይህንን በአገርና በሕዝብ ላይ የሚፈጸም በደል ዝም ብለው ማየታቸው ገዳዩን ሥርዓት እንደ ተባበሩ ያሳይባቸዋል የሚሉ በዝተዋል ። «በጎን ነገር አውቆ ለማይሠራው በደል ይሆንበታል» እንደ ሚለው የመጽሐፍ ቃል መሆኑ ነው። [iii]

3) አንድ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ስለ ነጻነት እንዲህ ይላል «ለሰው ልጅ ነፍስ ፣ ሳትገደድ ፥ ሳይፈረድባት ፥ የወደደችውን ታደርግ ዘንድ ነጻነት ተሰጣት (በተፈጥሮ ማለት ነው) መልካምነቷም ሆነ ክፉነቷ በራሷ ፈቃድ የተከናወነ ይሆን ዘንድ» ይላል ። [iv] «Freedom is the power or right to act, speak, or think as one wants without hindrance or restraint, and the absence of a despotic government» [v] የሚለው የእንግሊዝኛ ፍች በግእዝ “*ወገብረ ላቲ ሥልጣነ በውስቴታ ትግበር በከመ ኃርየት ፣ እንዘ አልቦ ዘይኬንና ፥ ወዘይሄይላ ፥ ከመ ይኩን ሠናያቲሃ ወእከያቲሃ በሥምረተ ሕሊናሃ በአምሳለ መላእክት*” ። (መቅድመ ወንጌል) ከሚለው የግእዝ ጥቅስ (ከላይ በአማርኛ የተረጎመው ማለት ነው) ጋር ምንም አይነት የሐሳብ ልዩነት የለውም ። [vi] ይህን የነጻነት መርሀ መጋፋት ከሰውም ከእግዚአብሔርም ጋራ ያጣላል ። አሁን በአገራችን እየሆነ ያለውም ያ ነው ። ነጻነትን ለሰው ልጅ መንግሥትም ሆነ የሃይማኖት ተቋማት አልሰጡትም ። ሰው የተፈጠረው በነጻነት፣ ለነጻነት፣ ነጻ

ሁኖ ነው የተፈጠረው ። ሰው ከሰው ጋር በስምነት ሁሉን ነገር ማድረግ ይችል፤ የሰውን ነጻ ፈቃድ በመጠቀም ሰውን የገዥ መዶቦችም ሆኑ የእውቀት ሰዎች ፣ የወደዱትን እንዲወድ ፥ የጠሉትን እንዲጠላ ሊያደርጉት ይችላሉ ፤ ያ ማለት ግን ነጻነቱን አጣ ማለት አይደለም ። ነጻ ፈቃዱንና ነጻ አስተሳሰቡን በአስተሳሰብ ፣ በትምህርት ማርከው ፣ ግለሰቡ አምኖበት እስካደረገው ድረስ በፈቃዱ አደረገው ሊባል ይችላል ። ነገር ግን ሳይፈልግ ፥ ሳይፈቅድ ፥ ሳያምንበት ፥ እያስፈራሩ ፣ ቅድመ ሁኔታ እያስቀመጡ ፣ ይህን ካላደርክህ እንዲህ ትሆናለህ ፣ ይህን ካደረግህም እንዲህ ትደረጋለህ እያሉ ፣ ያለፈቃዱ አስገድደው ከያዙት ግን ነጻነነቱን አጣ ማለት ነው ። እግዚአብሔር እንኳ የፈጠረውን ሰው በፈቃዱ እንዲያመልከው እንጂ ተገዶ እንዲያመልከው አላደረገም ። ያ ቢሆን ኑሮ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ የሆነውን ነገር ባላደረጉም ነበር ። [vii] ሰው ሁልጊዜ በጎውን ከክፉው ነገር ለይቶ እዲመርጥ ይመከራል እንጂ በግዳጅ የሚጠቅመውንም ሆነ የሚጎዳውን ነገር እንዳያደርግ መገደድ የለበትም ። የሰውልጅ ለደረገው በጎ ነገር «መልካም አደረግህ » ለሰራው ክፉ ነገር ደግሞ «እንዴት ይህን ታደርጋለህ» የሚል የህሊና ሕግ ተሰጥቶታልና።[viii]

<u>**የነጻነትስ ዋጋው ስንት ነው?**</u>

ለሰው ልጅ ከነጻነት የበለጠ ትልቅ ነገር ስለሌለው የተፈጥሮ ሀብቱም ስለ ሆነ በቀላሉ ነጻነቱን አሳልፎ አይሰጥም ፤ ነጻነት በተፈጥሮ የተሰጠው የሰው ሕይወት እና የማንነት ክብር ስለ ሆነ ሰው ነጻነቱን ከሚያጣ የሕይወት ዋጋ መክፈልን ይመርጣል ፤ Patrick Henry “give me liberty or give me death” [ix] ያለው ለዚህ ነበር። በሕወሀት እጅ የወደቀው የኢትዮጵያ መንግሥትም ነጻነት እንፈልጋለን ያሉትን ዜጎቹን በመግደል ፥ በማፈን ፥ ቶርች በማድረግ ፥ ሞትን እንጂ ነጻነትን አልሰጣችሁም ሲላቸው የምንሰማው ፥ የምናየው ለዚህ ነው ። ነጻነት የሰብአዊ ማንነት መሠረት ሲሆን ፣ የነጻነት መወሰድ ደግሞ ሰብአዊ ክብርን ማጣት ስለ ሆነ ሰው ሁኖ በነጻነቱ ላይ የሚደራደር የለም ።

**በመሆኑም ስለ ነጻነት በምንነጋገርበት በዚህ ጊዜ** - ለምን የነጻነት ጥያቄ ጠየቃችሁ ብሎ አፋኙ የሕወሓት ሥርዓት የጎንደርን የገበያ ማዕከላት በካድሬዎቹ በኩል በእሳት እያቃጠለ ፣ ኮንሶዎቹን በምድራቸው ላይ እየገደለ ፤ ኦሮሞዎችን አፍኖ እየገረፈ ፣ የወልቃይትን ባላባቶች ዝክረ ስም ለማጥፋት እየሰራ ፣ ምድራቸው የእኔ ነው ብሎ በመቀማት ይህ ነው የማይባል ጥቃት እየፈጸመ ፣ በሽዎች የሚቈጠሩ አገር ተረካቢ ወጣቶችን እየገደለ ፣ በእስር ቤት

እያሰቃየ ባለበት ወቅትነው ። ስለ ነጻነት ዋጋ የምንነጋገረው ፥ ስለ ነጻነት በምጽፍበት በዚህ ሰዓት በጎንደር ከተማ የቅዳሜን ገባያ ያቃጠሉት ትግርኛ ተናጋሪ ሰዎች የቀሩትን የከታማይቱን ተቅዋማት ለማቃጠል ጥረት ሲያደርጉ በሕዝብ ተይዘው ዛሬ መስከረም 11 ቀንም 2009 ዓ/ም በመገናኛ ብዙኃን ይነገር ነበር [x]። ነጻነቴ መብቴ ይከበር ያለ ሕዝብ ከተማው በገዡ ፓርቲ ድጋፍ በተሰጣቸው ትግሬዎች ለ50 ለ60 ዓመታት የደከመበት ሀብቱ ንብረቱ እየተቃጠለ ነው ። ሕዝብ ነጻነትን ሀብት ለማድረግ እየተዋደቀ ነው ። ልጆቹ ለእስራትና ለሞት ፣ ሀብቱና ንብረቱ ለእሳት እየተሰጠ ዛሬም ሕዝባችን አስገድደህ ልትገዛኝ አትችልም በማለት ከገዳዩ ሥርዓት ጋር ለነጻነቱ እየተዋደቀ ነው ።ከዚህ አንጻር የነጻነት ዋጋ እጂግ የከበረ ነው ።

**በጎንደር እና በጎጃም** - ሕዝብ ዕለት ዕለት እየታፈነ ነው ። በጎንደር በአምባ ጊዮርጊስ በእብናት በበለሳ ብዙዎች ነጻነታቸውን ለመንጠቅ ከሚታገላቸው ገዳይ ኃይል ጋር እየተዋደቁ ነው ። ከዚህ አንጻር ስናየው የነጻነት ዋጋ እጅግ ውድ ነው ። ነጻነት የሕይወት መሠረት ስለ ሆነ የነጻነት ዋጋ ደም ነው ። ነጻት የሕይወት ትርጉም ስለ ሆነ ነጻነት የሚጠበቀው የሕይወት ዋጋ እየተከፈለ ነው ። ክርስቶስ የሰው ልጆችን መንፈሳዊ ነጻነት ያስገኘውም ሕይወቱን ስለ ተጠቁት አሳልፎ እከመስጠት ደርሶ የነጻነት ባላጋራ የሆነውን ስውር ኃይል ድል በመንሣት ነበር ። ስለዚህ የነጻነት ዋጋ የከበረ ዋጋ ነው ።

<u>የጎጥ ፖለቲከኞች ያንሸዋረሩት የነጻነት ትርጉም ፦</u>

የነጻነትን ትጉም የሚያንሸዋርሩ አንዳንድ ጠባብ የፖለቲካ አቀንቃኞች እንደሚሉት ነጻነት ማለት አንድ ክፍለ ሀገርን ወይም ክልልን ከእናት ሀገር መገንጠል ማለት አይደለም ። ከእናት ሀገር መገንጠል ነጻነትንና ብልጽግናን የሚያመጣ ቢሆን ኑሮ ዛሬ ኤርትራ ባለፈላት ነበር ። ነጻነት ማለት አንድ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ለይቶ ወደ ሥልጣን ማውጣት ሌላውን ማግለል አይደለም ። ያ ቢሆን ኑሮ ሕወሀት የሰላም እንቅልፍ በተኛ ነበር ።በአንድ ቋንቋ መናገር የነጻነት ምንጭ አይደለም ። ያ ቢሆን ሕወሀት የትግራይን ሕዝብ እየገደለ ፣ ብአዴን የአማራ ወጣቶችን እያፈነ ፣ ኦሕዴድ የኦሮሞ ወጣቶችን እያሰቃየ ፣ አይስስ በቋንቋው የሚናገሩትን እስላሞችና ክርስቲያኖችን እያረደ ባልተገኘም ነበር ። ነገር ግን ነጻነት ማለት እያንዳንዱ ሰው በተፈጥሮ የተሰጠው መብቱና ነጻነቱ ተጠብቆለት ፣ ሰው በሰውነቱ ብቻ ተከብሮ ከሌላው ጋር በፍቅርና በአንድነት ለመኖር ሲችል ነው ። ነጻነትን የሚገፍ መንግሥት ብቻ አይደለም ፣ አባወራ የሚስቱን የልጆቹን ነጻነት ይገፋል ፣ ሴት ልጅም የባሏን እና የልጆቿን መብት ታስነጥቃለች ፤ ነጻነት በሥጋና

በደም በተሳሰሩ ኅብረተ ሰቦች መካካልም ይደመሰሳል ። አንድ ሕዝብ ነጻነት አለው ወይም ነጻ ሕዝብ ነው የሚባለው የሁሉም ዜጎች ግላዊ ነጻነት ተከብሮ ፣ በነጻነት በእኩልነት በአንድነት በነጻነት የሚኖርባት ነጻ ሀገር ስትኖረው ነው ።

**ማጠቃለያ**

**የዜጎችን ነጻነት አለማክበር ማለት?**

✓ የሰውን ሰውነት አለመቀበል ማለት ነው ፤

✓ ሰውን ከእንስሳትና ከግዑዛን ጋራ ማስተካከል ነው ፣

✓ የራስን ክብር (የነጻነት ተጋፊውን ክብርም) ማሳነስ የተፈጥሮን ሕግ መሻር ነው ።

✓ እናንተ ለእኛ መጠቀሚያ እንጂ የተፈጠራችሁት አንዳችን ለአንዳችን በረከት ሁነን አልተፈጠርንም ፣ እኔ የማስፈልጋችሁን ያክል እናንተ አታስፈልጉኝም ብሎ ማሰብ ነው ፣

✓ እኔ ላንተ አውቅልሃለሁ ፣ ራስህ ስለ ራስህ እንድታውቅ ሁነህ አልተፈጠርክም ብሎ የሰውን ተፈጥሮ ከመስደብ ይቆጠራል ።

✓ ዜጎችን መናቅ ማዋረድ የተገኙበትን ኅብረ ተሰብ ክብር ዝቅ ማድረግ፣ የሀገርን ክብርና ታሪክም ማዋረድ ነው ።

**በአንጻሩ አንድ ዜጋ ነጻነቱ ሲከበር፡-**

1. ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ ይሆናል ፤ ምክንያቱም ነጻነቱን የሚጠቀም ሰው በነጻነት በወሰነው ውሳኔ ምክንያት ስለሚደርስበት ጥፋት እራሱን ያስተካክላል እንጂ በሌላው ላይ እጁን አያነሣም ። በነጻነት ወዶ ፈቅዶ ለሠራው ነገር ሌላውን እንዲከስ ሕሊናው አይፈቅድለትም ።

2. ልበ ሙሉ ነው ፥ ለእድገትና ለሥልጣኔ ይራመዳል ፤

3. ሌላውን አይከስም ፣ በአንጻሩ ስለ ሌሎች ያስባል ፤

4. ነጻነት የሌለው ሕዝብ ግን ስለ ሌሎች ለማሰብ አይችልም ። አገራችን ኢትዮጵያ ለሌሎች ነጻነት ምሳሌ ሁና የኖረችው ከቀኘ ገዘዎች ነጻ ሀገር ነጻ መንግሥት ነጻ ሕዝብ ስለ ነበራት ነው ።

ስለዚህ የነጻነት ዋጋ ውድ መሆኑን በማወቅ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአንድነት በመሰለፍ ፍትሕ ርትዕ የሰፈነባት ፥ የግለሰቦች መብትና ነጻነት የሚከበርባት ፥ አንድነቷ የተጠበቀ አገር እንድትሆን መሥራት ይጠበቅበታል ።

ይቆየን ።

ልዑለቃል አካሉ ዓለሙ (መጋቤ ሐዲስ)

mhleulekal@gmail.com

---

i http://ethsat.com/esat-radio-tue-20-sep-2016/

ii የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት 1972 ገጽ 122

iii ያዕ 4 ፥ 17

iv በግእዝ እንዲህ ተጽፋል "ወገብረ ላቲ ሥልጣነ በውስቴታ ትግበር በከመ ኃርየት ፣ እንዘ አልቦ ዘይኴንና ፥ ወዘይሄይላ ፥ ከመ ይኩን ሠናያቲሃ ወእከያቲሃ በሥምረተ ሕሊናሃ በአምሳለ መላእክት" ። (መቅድመ ወንጌል)

v https://www.google.com/#q=what+is+freedom

vi ዝኒ ከማሁ

vii ዘፍ 2 ፥ 17

viii ዘዳ 30 ፥ 19 ፤ ኢያሱ 24 ፥ 15 ፤ ሮሜ 2፥15፣1ዮሐ 3፥19

ix "Give me liberty, or give me death!" is a quotation attributed to Patrick Henry from a speech he made to the Virginia Convention on March 23, 1775, https://en.wikipedia.org/wiki/Give_me_liberty,_or_give_me_death!

x http://ethsat.com/esat-radio-thu-22-sep-2016/